**ከአቶ ኃይለ-ኢየሱስ የደረሰን እ-ጦማር፦**

እንደምን አላችሁ! የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች!

የምኖረው፡ በአዲስ አበባ ሲኾን፣ የእናንተን የፌስቡክ ገጽ መከታተል ከጀመርኩ ከኹለት ዓመታት በላይ ኾኖኛል።

በመኾኑም፡ ከፌስቡክ የአገልግሎቱ ሥርጭት ባለፈ ለማወቅ ፍላጎቱ ስላደረብኝ፡ አገልግሎታችሁ በሚሰጥበት አድራሻ መከታተል እንድችል፡ የምትገኙበትን አድራሻ እንድታሳውቁን፡ በእግዚአብሔር ስም እለምናለሁ።

**ለአቶ ኃይለ-ኢየሱስ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ፦**

ይድረስ፦ ለተከበሩ አቶ ኃይለ-ኢየሱስ፤

በእግዚአብሔር ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን አቀርብልዎታለሁ።

"በእግዚአብሔር ስም እለምናለሁ!" ሲሉ፡ በተቀደሰው ክብረ-ቃል፡ ላቀረቡልን ጥያቄዎ፤ የምሰጥዎ መልስ፡ ከዚህ የሚከተለው ይኾናል፦ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በመላዎቹ የሰማይና የምድር ፍጥረታተ-ዓለማት ዘንድ ሞልታ የምትገኝ ስለኾነች፣ የተወሰነ እና የተከለለ መደበኛ አድራሻ የላትም፤ አያስፈልጋትምም። በየትኛውም፣ በኹሉም ቦታ ስለአለች ነው፤ ስለምትገኝም ነው።

አድራሻ ቢኖራትም፣ ቢያስፈልጋትም፡ አድራሻዎቿ፡ እያንዳንዶቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቿ የኾኑት፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ናቸው። እርሷ፡ የምትገኘው እና የምትኖረው፣ የምትሠራው እና የምትገለጠው፡ በዚያ፡ በእያንዳንዳቸው ሕያው ሰውነት ነውና።

አክባሪዎ፦ ኪዳናዊ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
[ንቡረ-እድ፡ ዘአክሱም ጽዮን።]
የኢትዮጵያ እግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ።